# ትምህርት 54

1. ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን በእግዚአብሔር ቃል ከማመን ይልቅ፣ ምን ለማየት ፈለጉ?

ሀ- ተአምራዊ ምልክት ለማየት ፈለጉ።

2. ፈሪሳውያኑና የሕግ መምህራን ተጨማሪ ተአምራዊ ምልክቶችን ለማየት የፈለጉት ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን ስላላመኑ ነበር።

3. «የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን የምናምነው ተአምራዊ ምልክት ካየን ብቻ ነው» ካልን፣ ምን ማለታችን ነው?

ሀ - «የእግዚአብሔር ቃል ውሸት ነው» ማለታችን ነው።

4. ኢየሱስ ለሰዎች «እሰጣቸዋለሁ» ያለው አንድ ብቸኛ ምልክት ምን ነበር?

ሀ- የዮናስ ምልክት።

5. የዮናስ ምልክት ምን ነበር?

ሀ- ዮናስ በትልቅ ዓሣ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቆየ ሁሉ፣ ኢየሱስም በምድር ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይቆያል።

ለ- ልክ እግዚአብሔር ዮናስን ከትልቅ ዓሣ ሆድ ውስጥ ከሦስት ቀንና ከሦስት ሌሊት በኋላ እንዳወጣው እንዲሁ፣ ኢየሱስንም ከምድር ሆድ ውስጥ ከሦስት ቀንና ከሦስት ሌሊት በኋላ ያወጣዋል።

6. ኢየሱስ «አይሁዶች ከነነዌ ሰዎች የበለጠ ክፉዎች ናቸው» ያለው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም የነነዌ ሰዎች የዮናስን ትምህርት ሰምተው ንስሐ ገብተው፥ አይሁዶች ግን የአዳኙን አምላክ የኢየሱስን ትምህርት ሰምተው ንስሐ ስላልገቡ ነው።

- ፈሪሳውያን ኢየሱስን ይጠሉት የነበረው ለምንድን ነው?
- ምክንያቱም ኢየሱስ፥ እርሱ አዳኙ አምላክ መሆኑን ስለነገራቸው።

- ፈሪሳውያን ኢየሱስ ሰው ብቻ ነው ብለው ያስቡ ነበር።

- ፈሪሳውያን ማንም ሰው «እኔ እግዚአብሔር ነኝ» ማለት አይገባውም ብለው ያስቡ ነበር።

- ፈሪሳውያን ኢየሱስን በሌላ በምን ይጠሉት ነበር?

- ኢየሱስ ኃጢተኞች መሆናቸውንና ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ስለነገራቸው።

- ፈሪሳውያን በኃጢአት መወለዳቸውን አያምኑም ነበር።

- ፈሪሳውያን በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ኃጢአት ሰርተው እንደማያውቁ ያምኑ ነበር።

- ፈሪሳውያን ኢየሱስን በሌላ በምን ይጠሉት ነበር?
- ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ይከተሉት ስለነበር በመቅናት።

- ፈሪሳውያን ሕዝቡ ከኢየሱስ ይልቅ እነርሱን መስማት እንዳለበት ያስቡ ነበር።

- ፈሪሳውያን ሕዝቡ ከኢየሱስ ይልቅ እነርሱን መከተል እንዳለበት ያስቡ ነበር።

- ፈሪሳውያን ኢየሱስን ይጠሉት ስለነበር ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ትእዛዞች አንዱን እንኳን ያፈርስ ይሆናል ብለው በትኩረት ይከታተሉት ነበር።

- ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ትእዛዞች አንዱን ቢያፈርስ ፈሪሳውያን ምን ያደርጉ ነበር?
- ኢየሱስን በሞት ይቀጡት ነበር።

- ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ትእዛዞች አንዱን እንኳን አፍርሷል?
- አላፈረሰም።

- ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ትእዛዞች አንዱን እንኳን በፍጹም ያላፈረሰው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ፍጹም ስለሆነ ነው።
- ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ነው።

- ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት ስለሆነ ነው።
- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን በሁሉም ነገር ስለታዘዘ ነው።

- ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንጂ ፈሪሳውያንን አልታዘዘም።

- ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ያልታዘዘው ለምንድን ነው?
- ምክንያቱም ፈሪሳውያኑ የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ስለለወጡ ነው።

- ፈሪሳውያኑ የእግዚአብሔርን ሕግጋት የለወጡት እንዴት ነበር?

- ፈሪሳውያን የለወጡት፥የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ውሸታም በማድረግ፥ በእግዚአብሔር ትእዛዞች ላይ የራሳቸውን ሕጎች በመጨመር ነው።

- ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ትእዛዞች ላይ የራሳቸውን ሕጎች በመጨመራቸው፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ውሸታም አድርገዋል።

- ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ትእዛዞች ላይ ከጨመሩት ሕጎች አንዱ፣ «በሰንበት ቀን ማንም ሰውን መፈወስ የለበትም» የሚል ነበር።

- ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ትእዛዞች ላይ ይህን ሕግ የጨመሩት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እነርሱ «አንድን ሰው መፈወስ ሥራ መሥራት ነው፣ እግዚአብሔር ደግሞ በሰንበት እንድንሠራ አይፈልግም» ስለሚሉ ነው።

- ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ የጨመሩት ሕግ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ውሸታም አደረገው።

- በአንድ የሰንበት ቀን፣ ኢየሱስ ወደ ምኩራብ ገባ።

ማርቆስ 3፡1-2

1- ኢየሱስ በሌላ ጊዜ ወደ ምኩራብ ገባ፤ በዚያም እጁ የሰለለች ሰው ነበር።

2- በምክንያት ሊከሱት የሚፈልጉ ሰዎችም በሰንበት ቀን ይፈውሰው እንደ ሆነ ለማየት ይጠባበቁ ነበር።

- ኢየሱስ ወደ ምኩራብ በገባ ጊዜ እጁ የሰለለች ሰው በዚያ ነበር።

- ፈሪሳውያን ኢየሱስን በትኩረት ይመለከቱት የነበረው ለምንድን ነው?

- ኢየሱስ ሰውየውን በሰንበት ቀን ይፈውሰው እንደ ሆነ ለማየት ስለፈለጉ?

- ሰውየው በሰንበት ቀን ቢፈወስ እግዚአብሔር ይቆጣ ነበር?
- አይቆጣም።

- ኢየሱስ ሰውየውን በሰንበት ቀን ቢፈውሰው እግዚአብሔር የማይቆጣው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም አንድን ሰው በሰንበት ቀን መፈወስ ሥራ መስራት ስላልሆነ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ሰውየውን እንዲፈውሰው ስለፈለገ ነው።

- ኢየሱስ ምን አደረገ?

ማርቆስ 3፥3-5

3- እርሱም እጁ የደረቀችውን ሰው፣ «በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ተነሥተህ ቁም» አለው።

4- ኢየሱስም «በሰንበት ቀን የተፈቀደው መልካም ማድረግ ነው ወይስ ክፉ? ሕይወት ማዳን ነው ወይስ ማጥፋት?» አላቸው። እነርሱ ግን ዝም አሉ።

5- በልባቸው ደንዳናነት አዝኖ በዙሪያው የቆሙትን በቍጣ ተመለከታቸውና ሰውየውን፣ «እጅህን ዘርጋ!» አለው፤ ሰውየውም እጁን ዘረጋ፤ እጁም ፍጹም ደኅና ሆነችለት።

- ኢየሱስ በፈሪሳውያን ላይ የተቆጣው ለምን ነበር?

- ኢየሱስ የተቆጣው፥የልባቸውን ደንዳናነት አይቶ ነው።

- ኢየሱስ ልባቸው ደንዳና መሆኑን እንዴት አወቀ?

- ኢየሱስ የሰውን ልብ ሁሉ መመልከት ይችላል።

- ኢየሱስ የሰውን ልብ ሙሉ በሙሉ ያውቃል።

- ኢየሱስ የፈሪሳውያንን ልብ ሲመለከት እነርሱ እግዚአብሔር የሚያስተምራቸውን ለመስማት እንደማይፈልጉ አየ።

- እግዚአብሔር የሚያስተምረንን ለመስማት አለመፈለግ ትልቅ ስሕተት ነው።

- ፈርዖን እግዚአብሔር የሚያስተምረውን መስማት ባለመፈለጉ፣ እግዚአብሔር በሞት ቀጣው።

- እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ እግዚአብሔር የሚያስተምራቸውን ለመስማት ባለመፈለጋቸው እግዚአብሔር በሞት ቀጣቸው።

- እግዚአብሔር የሚያስተምራቸውን ለመስማት የማይፈልጉትን ሰዎች ሁሉ በሞት ይቀጣቸዋል።

- ኢየሱስ እጁ የሰለለችውን ሰው ፈወሰው?

- አዎን።

- እጁ የሰለለውን ሰው መፈወስ የሚችል ማን ብቻ ነበር?

- እግዚአብሔር ብቻ።

- ኢየሱስ እጁ የሰለለችበትን ሰው በምን ፈወሰው?

- በመናገር ብቻ።

- በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር ምድርን እንዴት ፈጠረ?
- በመናገር ብቻ።

- ኢየሱስ ምድርን የፈጠረው በመናገር ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ እጁ የሰለለችውንም ሰው የፈወሰው በመናገር ብቻ ነበር።

- ኢየሱስ እጁ የሰለለችውን ሰው ከፈወሰው በኋላ፣ ፈሪሳውያን ምን አደረጉ?

ማርቆስ 3፥6

6- ፈሪሳውያንም እንዴት ሊያጠፉት እንደሚችሉ ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት ጋር መመካከር ጀመሩ።

- ከምኩራብ ወጥተው ኢየሱስን እንዴት እንደሚገድሉት መመካከር ጀመሩ።

- ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለመግደል የተመካከሩት ከማን ጋር ነበር?
- ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት ጋር።

- ከሄሮድስ ወገን የሆኑት እነማን ነበሩ?

- ከሄሮድስ ወገን የሆኑት የንጉሥ ሄሮድስ ተከታዮች ነበሩ።

- ከሄሮድስ ወገን የሆኑት ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን አያምኑም ነበር።

- ይህ ንጉሥ ሄሮድስ ኢየሱስ ሕጻን ልጅ ሳለ ሊገድለው የሞከረው የንጉሥ ሄሮድስ ልጅ ነበር።

- ሕዝቡ ኢየሱስ የሚሠራቸውን ተአምራት በሰሙ ጊዜ፣ ምን አደረጉ?

ማርቆስ 3፡8

8- ኢየሱስ የሚሠራውን ነገር የሰሙ ሰዎችም ከይሁዳ፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከኤዶምያስ፣ በዮርዳኖስ ማዶ ካለው አገር እንዲሁም ከጢሮስና ከሲዶና አካባቢ ወደ እርሱ መጡ።

- ብዙ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጡ።

- የኢየሱስን ትምህርት ሊሰሙ መጡ።
- ከበሽታቸው ሊፈወሱ መጡ።

- ኢየሱስ ሰዎችን መፈወስ እንደሚችል ያውቁ ነበር።
- ሰዎችን መፈወስ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ሰዎች ወደ ኢየሱስ ስለመጡ፣ ብዙ ሕዝብ ወደ ኢየሱስ ተሰበሰበ።

ማርቆስ 3፡9-10

9- የተሰበሰበውም ሕዝብ እንዳያጨናንቀው አነስተኛ የሆነ ጀልባ እንዲያዘጋጁለት ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው።

10- ብዙዎችን ፈውሶ ስለ ነበር፣ በሕመም የሚሠቃዩ ሁሉ ሊዳስሱት ይሽቀዳደሙ ነበር።

- ብዙ ሕመምተኞች ወደ ኢየሱስ በመምጣት፥ ኢየሱስን በመንካት ብቻ ይፈወሱ ነበር።

- ሕዝቡ ኢየሱስን ለመንካት ይገፋፉ ስለ ነበር፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ጀልባ እንዲያዘጋጁለት ነገራቸው።

- ኢየሱስን የሚመስል አንድም ሰው የለም።
- ኢየሱስ ከሁሉም ይበልጣል።

- ርኩሳን መናፍስት ኢየሱስን ባዩት ጊዜ ምን አሉ?

ማርቆስ 3፡11

11- ርኩሳን መናፍስትም ባዩት ቊጥር ከፊቱ እየወደቁ፣ «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!» በማለት ይጮኹ ነበር።

- ርኩሳን መናፍስት ኢየሱስን ምን ብለው ጠሩት?
- የእግዚአብሔር ልጅ ብለው ጠሩት።

- ርኩሳን መናፍስት ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ብለው የጠሩት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ርኩሳን መናፍስት ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ መምጣቱን ስላውቁ ነው።

- ሰዎች ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱን ባያውቁም እንኳ ርኩሳን መናፍስት ግን እርሱ አዳኝ አምላክ መሆኑን አውቀዋል።

- ርኩሳን መናፍስት፥ ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን በምን አወቁ?

- ርኩሳን መናፍስት ክፉ ከመሆናቸውና ሰይጣንን ከመከተላቸው በፊት መልካም መላእክት ሳሉ ኢየሱስን በሰማይ አገልግለውታል።

- ሁሉም ርኩሳን መናፍስት ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ።
- ይሁን እንጂ ርኩሳን መናፍስት በኢየሱስ እንድታምኑ አይፈልጉም?

- ርኩሳን መናፍስት በኢየሱስ እንድታምኑ የማይፈልጉት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ከእነርሱ ግዛት እንዲታመልጡ ስለማይፈልጉ ነው።

- በኢየሱስ ካመናችሁ፤ ኢየሱስ ከርኩሳን መናፍስት ኃይል ነፃ ያወጣችኋል።

- ኢየሱስ ርኩሳን መናፍስትን ምን ብሎ አዘዛቸው?

ማርቆስ 3፡12

12- እርሱ ግን ማንነቱን እንዳይገልጹ አጥብቆ ይገሥጻቸው ነበር።

- ኢየሱስ ርኩሳን መናፍስት ስለ እርሱ ማንነት ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው።

- ኢየሱስ ርኩሳን መናፍስት ስለ እርሱ ማንነት እንዲናገሩ ያልፈለገው ለምን ነበር?

- ኢየሱስ ሰዎች ከእርሱ ሰምተው በእርሱ እንዲያምኑ እንጂ ከርኩሳን መናፍስት ሰምተው በእርሱ እንዲያምኑ ስላልፈለገ ነው።

- ኢየሱስ ሰዎች የእርሱን ቃል ሰምተው እንዲያምኑ እንደሚፈልግ ሁሉ እግዚአብሔርም የእርሱን ቃል ሰምተን በኢየሱስ እንድናምን ይፈልጋል።

- ኢየሱስ ሕዝቡን መፈወስ ካበቃ በኋላ፣ ወደ ተራራ ወጣ።

ማርቆስ 3፡13-19

13- ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ የሚፈልጋቸውን ወደ እርሱ እንዲመጡ ጠራቸው። እነርሱም ወደ እርሱ መጡ።

14- ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለቱን ሾማቸው፤ ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው፤

15- አጋንንትን እንዲያስወጡም ሥልጣን ሰጣቸው።

16- የሾማቸውም ዐሥራ ሁለቱ እነዚህ ናቸው፤ ጴጥሮስ ብሎ የጠራው ስምዖን፣

17- ቦአኔርጌስ ይኸውም፣ «የነጐድጓድ ልጆች» ብሎ የጠራቸው የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ፤

18- እንድርያስ፤ ፊልጶስ፣ በርቶሎሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ ቶማስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ታዴዎስ፣ ተቀናቃኙ ስምዖን፣

19- እንዲሁም አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ።

- እርሱን ከተከተሉት ሰዎች መካከል፣ የእርሱ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ኢየሱስ የመረጣቸው ስንቱን ነበር?

- ዐሥራ ሁለቱን።

- እነዚህ ዐሥራ ሁለት ሰዎች ማን ተብለው ይጠሩ ነበር?

- ሐዋርያት።

- ኢየሱስ የመረጣቸው ሐዋርያት በደንብ ማንበብም ሆነ መጻፍ የማይችሉና ብዙ ገንዘብ ያልነበራቸው ነበሩ።

- ኢየሱስ ዐሥራ አንዱን ሐዋርያት የመረጠው በእርሱ ስላመኑ ነው።
- ኢየሱስ ከመረጣቸው ሰዎች መካከል አንዱ ይሁዳ ይባላል።

- ይሁዳ በኢየሱስ አምናለሁ ቢልም፥ እምነቱ የአፍ ብቻ ነበር።

- በልቡ በኢየሱስ አላመነም ነበር።

- ሌሎቹ ዐሥራ አንድ ደቀ መዛሙርት ይሁዳ በኢየሱስ ያላመነ ሰው መሆኑን አያውቁም ነበር ኢየሱስ ግን ያውቅ ነበር።

- እንዲሁም ኢየሱስ ይሁዳ አንድ ቀን እርሱን አሳልፎ እንደሚሰጠው ያውቅ ነበር።

- ምናልባት እኛ ሰዎችን ልናታልላቸው እንችል ይሆናል።

- ምናልባት እኛ እንደ ይሁዳ «በእግዚአብሔር አምናለሁ» በማለት ሰዎችን ልናታልላቸው እንችል ይሆናል።

- እግዚአብሔርን ግን ፈጽሞ ልናታልለው አንችልም።

- እግዚአብሔር ልባችንን ይመለከታል።